# መልክአ ማርያም

ሰላም ሰላም ለዝክረ ስምኪ ሐዋዝ፣ እምነ ከልበኔ ወቀሎስጥ ወእምነ ሰንበልት ምዑዝ፣ ማርያም ድንግል ለባሲተ ዐቢይ ትዕዛዝ፣ ይስቅየኒ ለለጽባሑ ወይነ ፍቅርኪ አዚዝ፣ ከመ ይስቅዮ ውኂዝ ለሠናይ አርዝ።

እመቤቴ ማርያም ሆይ እጅግ ለሚያምረው ስም አጠራርሽ ሰላምታ ይገባል። ከልበኒ ቄስጥ ሰንበልት ከሚባሉ ሽቶች እጅግ የተወደደ መዓዛ አለውና። ድንግል ሆይ ከሥላሴ ዘንድ ታላቅ ክብርን የተጎናጸፍሽ ነሽ። መልካም ተክል በመስኖ ውሃ እንዲለመልም። በመውደድሽ ወይን ነፍሴ ከጽድቅ ጥሟ በየጊዜው ትርካ።

ሰላም ለሥዕርተ ርእስኪ ዘተንእደ ዕፍሮሁ፣ ለአቡኪ በከናፍሪሁ፣ ማርያም ድንግል ለእግዚአብሔር ጽርሑ፣ ለገብርኪ እግዝእትየ ኢትኅድግኒ እላሑ፣ ከመ ኢይበሉኒ ፀር አይቴኑመ ምክሑ።

እመቤቴ ማርያም ሆይ አወራረዱ ከገለዓድ ተራራ እንደሚወርድ ፍየል መንጋ ለተጅመለመለው የራስ ፀጉርሽ ሰላምታ ይገባል። አስቀድሞ በአባትሽ አፍ እንደተነገረ። ድንግል ሆይ የእግዚአብሔር ማደሪያ ንጹሕ አዳራሽ ነሽ። ጠላቶቼ ያች የሚመካባት እመቤቱ ወዴት አለች ብለው እንዳይዘባበቱብኝ። እኔን ባሪያሽን ለኃዘን ለትካዜ አሳልፈሽ አትስጭኝ።

ሰላም ለርእስኪ በቅብዐ ቅዳሴ ርሑስ፣ አኮ አኮ በቅብዐ ደነስ፣ ማርያም ድንግል ንጽሕተ ሥጋ ወነፍስ፣ ያንጽሐኒ እምነ ርኩስ፣ ምፍሕመ ቍርባኑ ቅዱስ፣ አዝዚዮ ለሱራፌ ዘሰማይ ቀሲስ።

እመቤቴ ማርያም ሆይ የዚህን ዓለም ቅብዐ ዘይት ያይደለ። የምስጋና ሽቱ መቀባት ለተገባው ራስሽ ሰላምታ ይገባል። ድንግል ሆይ በነፍስ በሥጋ በውስጥ በአፍኣ ንጽሕት ነሽ። እኔን ኃጥኡን ባሪያሽን በቅዱስ ቍርባኑ ፍሕም ያነፃኝ ዘንድ። ሰማያዊዉን ቄስ ሱራፌን እዘዥልኝ።

ሰላም ለገጽኪ ዘጥቀ ይልሂ፣ እምሥነ ከዋክብት ወወርኅ ወእምስነ ፀሐይ መብርሂ፣ ማርያም ድንግል ፍናዋትየ ሠርሂ፣ በመዓልት ወበሌሊት ኢይርከበኒ ጸናሒ፣ መሥገርተ አበሳ ዘይጠፍር ወግበ ዘይድሂ።

እመቤቴ ማርያም ሆይ ብርሃነ መለኮት ፈጽሞ ለተዋሐደው ለፊትሽ ፀዳል ሰላምታ ይገባል። ከፀሐይ ከጨረቃ ከከዋክብትም እጅግ አንፀባራቂ ነውና። ድንግል ሆይ የመግቢያ መውጫዬን ጎዳና ጥረጊልኝ። በመዓልትና በሌሊት ከሚያሸምቅ ማጅራት መቺ ጠብቂኝ። እሱ የተንኮል ወጥመዱን አጥምዶ ጉድጓዱን ቆፍሮ ይጠብቀኛልና።

ሰላም ለቀራንብትኪ ደመናተ ብካይ እለከና፣ አመ አሕመመ ወልደኪ ቅንአተ ቀያፋ ወሐና፣ ማርያም ድንግል ለባሲተ ንጽሕ ወቅድስና፣ አስምዕኒ ነገረ ጽድቅ ዘያስተፌሥሕ ሕሊና፣ ከመ አስተፍሥሐኪ ጥቀ ዘመልአክ ዜና።

እመቤቴ ማርያም ሆይ ልዩ ለሆኑ ለዓይኖችሽ ቀራንብት ሰላምታ ይገባል። የቀያፋና የሐና ቅንዓት ልጅሽን ባሳመመ ጊዜ ዕንባን የቋጠረ ደመና ሆነዋልና። ድንግል ሆይ ንጽሕናን ቅድስናን የተጎናፀፍሽ ነሽ ፀዋሬ ዜና ገብርኤል በብሥራቱ ደስ እንዳሰኘሽ። ልቡናዬን ደስ የሚያሰኝ ነገር አሰሚኝ።

ሰላም ለአዕይንትኪ ዘተመሰላ አብያዘ፣ እለ ይፌጽማ ትእዛዘ፣ ማርያም ድንግል እንተ ኢተአምሪ ኃእዘ፣ ናዝዝኒ በንባብኪ እመ ልብየ ተከዘ፣ በሐብለ ሰቆቃው ጽኑዕ ኢይኩን እኑዘ።

እመቤቴ ማርያም ሆይ እንደጥቅምት ውሃ ለጠሩ እንደ አጥቢያ ኮከብ ለሚያበሩ ዓይኖችህ ሰላምታ ይገባል። ድሀ አደጉንና ችግረኛውን ይመለከታልና። ድንግል ሆይ ኑፋቄ ልቡና ሐኬተ ህሊና የሌለብሽ ፍጽምት ነሽ። በፅኑ የልቅሶ ገመድ የተተበተብኩ እንዳልሆን ልቤ ባዘነና በተከዘ ጊዜ ታረጋጊኝ ዘንድ ፈጥነሽ ድረሽ።

ሰላም ለአዕዛንኪ እለ ሰምዓ ቃሎ፣ አግዚአብሔር እግዚእ ሶበ ለገብርኤል ተመሰሎ፣ ማርያም ድንግል ጽሕቅት ለተሣህሎ፣ ሶበ ለልብየ እሳተ ኀዘን አሕለሎ፣ ይጽምዓኒ እላ ነገርየ ኵሎ።

እመቤቴ ማርያም ሆይ ንጹሓን ለሆኑ ጆሮችሽ ሰላምታ ይገባል። የሁሉ ጌታ እግዚአብሔር በገብርኤል ተመስሎ በመጣ ጊዜ ሁሉን ለመስማት በቅተው ተገኝተዋልና። ድንግል ሆይ ለይቅርታና ለቸርነት የተጋሽ ስለሆንሽ። ልቤ በኃዘን እሳት በተቃጠለ ጊዜ ቸልተኝነት የሌለባቸው ጆሮችሽ ነገሬን ያድምጡ።

ሰላም ለመላትሕኪ በእሳተ አንብዕ እለ ውዕያ፣ ጊዜ ሰቀሉ በኵረኪ ውሉደ ራኄል ወልያ፣ ማርያም ድንግል ለነፍስየ

እመቤቴ ማርያም ሆይ የራሔልና የልያ ልጆች ልጅሽን በሰቀሉት ጊዜ። በእሳት እንባ ለተቃጠሉት ጉንጮችሽ ሰላምታ

ደብረ ምስካያ፣ አድኅንኒ እምአፈ ደም ዘአናብስተ ሐቅል አርአያ፣ ከመ ማሕፈድ ጠቢብ ወምእመን ኬንያ።

ይገባል። ድንግል ሆይ እጅግ በታመነው በተደነቀው የጥበብሽ ስልት የደም ወገን ከሚሆን ከዱር አንበሳ (ዲያብሎስ) አድኚኝ። የነፍሴ አምባ መጠጊያ አንቺ ነሽና።

ሰላም ለአዕናፍኪ መሳክወ ሠናይ መዐዛ፣ ይኄይስ ፈድፋደ እምጼና ስኂን ዘጠረጴዛ፣ ማርያም ድንግል ለሕይወትየ ምርጉዛ፣ ሰዋስው ዘምድረ ሎዛ፣ እንተ ርእየኪ ወሬዛ፣ አመ ዕለተ ፍዳ ኩንኒ ቃውመ ወቤዛ።

እመቤቴ ማርያም ሆይ መልካም መዓዛ ያለው የሽቱ መፍለቂያ ለሚሆኑ አፍንጮችሽ ሰላምታ ይገባል። ክቡር ከሆነ ከጠረጴዛ ዕጣን ሽታ መዓዛው የተለየ ነውና። ድንግል ሆይ ያዕቆብ በፍኖተ ሎዛ በወርቅ መሰላል አምሣል እንዳየሽ። ለኔም የሕይወቴ መሸጋገሪያ ድልድይና ምርኩዜ ነሽ። ስለዚህም በፍርድ ቀን ዋስ ጠበቃ ትሆኚኝ ዘንድ እማልድሻለሁ።

ሰላም ለከናፍርኪ ከመ ፍሕሶ ቀይሕ፣ ሥርጉተ ቅዳሴ ወንጽሕ፣ ማርያም ድንግል ሞኅተ ጽባሕ፣ ባልሕኒ እምነ ወይሌ ወአንግፍኒ እምላሕ፣ እስመ ለልብየ ኀዘኑ ብዙኅ።

እመቤቴ ማርያም ሆይ ቀይሐን የፍሕሦ አበባ ለሚመስሉ ከናፍሮችሽ ሰላምታ ይገባል። በንጽሕና በቅድስና የተጌጡ ናቸውና። ድንግል ሆይ የእውነተኛው ብርሃን መውጫ የምስራቅ ደጃፍ አንቺ ነሽ። ከኀዘን ከልቅሶ ፈጽመሽ አድኚኝ። የልቤ ኀዘን ብዙ ነውና።

ሰላም ለአፉኪ ዘሰዐመ ርስነ፣ እንዘ አበአዕሩግ ውእቱ በጊዜ ኮነ ሕፃነ፣ ማርያም ድንግል ዘትጼንዊ ስኂነ፣ ኀፍረተ አበሳ ሶበ ገጽየ ተከድነ፣ ለናዝዞትየ እሙ ብጽሒ ፍጡነ።
ሰላም ለአስናንኪ ሐሊበ ዕጉልት ዘተዛወጋ፣ ወመራዕየ ቅሩፃተ እለ እምሕፃብ ዐርጋ፣ ማርያም ድንግል ለደብተራ ስምዕ ታቦተ ሕጋ፣ አፍቅርኒ እንበለ ንትጋ፣ ለብእሴ ደም ወሥጋ፣ ዘየዐቢ እምዝ ኢየኀሥሥ ጸጋ።

እመቤቴ ማርያም ሆይ የአረጋውያን አባት ሲሆን ከአንቺ ሰው ሆኖ ሕፃን በነበረበት ጊዜ ፍሕመ መለኮትን ለሳመ አፍሽ ሰላምታ ይገባል። ድንግል ሆይ እንደ ንጹሕ ዕጣን መዓዛ ያለሽ ነሽ። የበደልን ኃፍረት ፊቴ በተከናነበ ጊዜ። እናት ሆይ በደሌን አጥፍተሽ ታረጋጊኝ ዘንድ ፈጥነሽ ድረሽ።

እመቤቴ ማርያም ሆይ ምሳሌ በታጣላቸውም የጊደር ወተት ለሚኀራበታቸው ጥርሶችሽ ሰላምታ ይገባል። ከተሸለቱ በኋላ ታጥበው እንደነፁ መንጐች ፅዕድዋን ናቸውና። ድንግል ሆይ የደብተራ ኦሪት የሕግ ምስክሯ ነሽ። ልጅሽ ደም አርግቶ አጥንት ሰክቶ የፈጠረኝን እኔን አጥብቀሽ ፈልጊኝ። ከዚህ የበለጠ ጸጋ አልሻምና።

ሰላም ለልሳንኪ ሙኀዘ ሐሊብ ወመዓር፣ ዘተነብዮ ወፍቅር፣ ማርያም ድንግል ወለተ ድኅኃን አድባር፣ ኅብእኒ እምዐይነ ፀር፣ ወአንጽሐኒ እምነውር፣ እስመ ተስፋየ አንቲ በሰማይ ወምድር።

እመቤቴ ማርያም ሆይ የመዓርና የወተት መፍለቂያ ለሆነው አንደበትሽ ሰላምታ ይገባል። ይኸውም የፍቅር አንድነት መገኛ ነው። ድንግል ሆይ ከኢያቄምና ከሐና በሕግ የተገኘሽ ቡርክት ልጅ ነሽ። እኔን ባሪያሽን ከጠላት ዓይን ሠውሪኝ ከነውርም ንጹሕ አድርጊኝ። በሰማይም በምድርም ተስፋዬ አንቺ ነሽና።

ሰላም ለቃልኪ እምአስካለ ወይን ጥዑም፣ ወእምድምፀ ናብሊስ አዳም ዘያረስዖ ለሕማም፣
ማርያም ድንግል ዘብርሃነ ሕይወት ተቅዋም፣ እመ ተዐውከ በላዕሌየ ማዕበለ ዝንቱ ዓለም፣ ከመ ያርምም ንሥኢዮ መሐሪት እም።

እመቤቴ ማርያም ሆይ ከወይን የፍሬ ዘለላ ይልቅ ለሚጥመው ቃልሽ (አነጋገርሽ) ሰላምታ ይገባል። ሕማምን ከሚያስረሳ ከበገና ድምፅ እጅግ ያማረ ነውና። ድንግል ሆይ የሕይወት ብርሃን መቅረዝ አንቺ ነሽ። የዚህ ዓለም ፍቅር ሞገዱን በላዬ ላይ ቢያነሣብኝ። ይቅር ባይ እናት ሆይ ፀጥ ይል ዘንድ ገስጪው።

ሰላም ለእስትንፋስኪ ዘመአዛሁ ሕይወት፣ ከመ መዐዛ ዕፅ ኀሩይ ዘውስተ ገነት፣ ማርያም ድንግል ቤተ ቅድሳት፣ ጽንሕኒ ውስተ ሠናይ ወሠውርኒ እሞት፣ በአክናፍኪ ርግብየ ኅሪት።

እመቤቴ ማርያም ሆይ መዓዛው ሕይወትን ለሚያድሰው እስትንፋስሽ ሰላምታ ይገባል። በገነት እንደሚገኝ እንደተመረጠ የሽቱ ዛፍ ልዩ መዓዛ አለውና። ድንግል ሆይ ቅዱሳንን ለሚቀድስ ማደሪያ ሆነሽ መልካሟ ርግብ ሆይ በመልካም ጉዳና መርተሽ ከሞት ሠውሪኝ በክንፈ ረድኤትሽ ጥላ ሥርም ሸሽጊኝ።

ሰላም ለጉርዔኪ ሠናይ እምወይን፣ በከመ ይቤ ሰሎሞን፣ እመቤቴ ማርያም ሆይ አስቀድሞ ሰሎሞን እንደተናገረ።

ማርያም ድንግል ለባሲተ ዐቢይ ብርሃን፤ ክድንኒ ገርዜነ ጸጋ ኢያዕጽበኒ ዕርቃን፤ ዘኢአነምዎ ጠቢባን በኪን::

ከወይን የሚጥሙ ቃላት ለሚፈልቁበት ጉሮሮሽ ሰላምታ ይገባል:: ድንግል ሆይ ታላቁን ብርሃናዊ መጐናጸፊያ የተጐናጸፍሽ ነሽ:: የጽድቅ መራቆት እንዳያስጨንቀኝ ጥበበኞች ያልተጠበቡትን ብልሃተኞች ያልደከሙበት የጸጋ ልብስ አልብሽኝ::

ሰላም ለክሳድኪ ቃማ ንጽሕ ዘዐነቀ፤ ከመ አዋልድ አኮ ብሩረ ወወርቀ፤ ማርያም ድንግል ዘተመሰልኪ ማዕነቀ፤ ሕይወትየ በንዝህላል እመ ተሰልጠ ወኀልቀ፤ ወስክኒ ክራማተ እስከ እገብር ጽድቀ::

እመቤቴ ማርያም ሆይ እንደሌሎች ደናግል የብርና የወርቅ ያይደለ:: የንጽሕናን ሐብል ለአጠለቀ አንገትሽ ሰላምታ ይገባል:: ድንግል ሆይ ፀአዳ በምትሆን ርግብ እንመስልሻለን:: የሕይወት ዘመኔ በስንፍናን በንዝህላልነት ሲያልቅ ቢቃረብ ንስሐ የምገባበት ጽድቅ የምሠራበት ዕድሜ ጨምሪልኝ::

ሰላም ለመታክፍትኪ እለ ግሑሣት እማንቱ፤ ለጊጋይ እምነ አርዑቱ፤ ማርያም ድንግል ለሆሴዕ ሠርጐ ትርሚቱ፤ በልኒ እግዝእትየ ጸሕቀ ሕሊናየ ዝንቱ፤ ፍኖተ የማን ይምራሕከ ወተአኵት ቦቱ::

እመቤቴ ማርያም ሆይ ኪሩቤል የሚሸከሙትን መለኮት ለተሸከሙ ትከሻችሽ ሰላምታ ይገባል:: ከበደል ቀንበር የራቁ ናቸውና:: ድንግል ሆይ የሆሴዕ የሽልማቱ ጌጥ ነሽ:: እመቤቴ ሆይ ልጅሽ ልቤ የተጨነቀበትን ነገር መፍትሔ ይፈልግልሀ:: አመስግነውም ዘንድ ቀና መንገድ ይምራህ በይኝ::

ሰላም ለዘባንኪ እምዘባነ ኪሩብ ዘዐብየ፤ ሐዚሎ እሳተ ወእምርስነ ነዱ ኢውዕየ፤ ማርያም ድንግል ፈጻሚተ ኵሉ ጸሕቅየ፤ ሀብኒ እግዝእትየ ዘተመነይኩ ሠናየ፤ እንበለ አዕርዖ ፍጡነ በጺሐኪ ዝየ::

እመቤቴ ማርያም ሆይ ከዘባነ ኪሩብ ለሚከብረው ዘባንሽ ሰላምታ ይገባል:: እሳትን ተሸክሞ የነበልባሉ ውዕየት አላቃጠለውምና:: ድንግል ሆይ ያለመዘግየት ፈጥነህ ድረሺልኝና:: ችግሬን ሁሉ አስወግጅልኝ:: እመቤቴ ሆይ የበጎ ነገር ምኞቴንም ፈጽሚልኝ::

ሰላም ለእንግድዓኪ ለእሳተ መለኮት ምርፋቁ፤ ዘይቄድስ ነፍሰ ወያጥዒ ሞቁ፤ ማርያም ድንግል ለነዳይ ንዋየ ወርቁ፤ እመ ነገደ ርኁቀ ወሐረ ዕራቁ፤ ኢያኀዝኖ ሲሳይ እስመ አንተ ስንቁ::

እመቤቴ ማርያም ሆይ የእሳተ መለኮት ማረፊያ ለሆነ ደረትሽ ሰላምታ ይገባል:: ይኸውም ሰውነትን የሚቀድስ መቀቱም ነፍስን የሚፈውስ ነው:: ድንግል ሆይ ለእግረኛ የወርቅ ገንዘቡ አንቺ ነሽ:: ሩቅ አገር ቢሔድ ቢራቆትም አያዝንም ልብስና ስንቁ አንቺ አለሽለትና::

ሰላም ለሕፅንኪ ለጥበብ ሰማይ ምዕራፋ፤ ዘኢይትረከብ ሱታፋ፤ ማርያም ድንግል ጸጋዊተ ሰላም ወተስፋ፤ ኵንኒ እግዝእትየ ቅድመ ፀርየ ሐገፋ፤ ከመ ያፍ አፍኀርቲሃ ትሴውር በክንፋ::

እመቤቴ ማርያም ሆይ ለሰማያዊት ጥበብ ማረፊያ ለሆነች ሕፅንሽ ሰላምታ ይገባል:: ተወዳዳሪ ወይም ምሳሌ አይገኝለትምና:: ድንግል ሆይ ፍቅር የተመላበት ተስፋን የመስጠት መብት አለሽ:: እመቤቴ ሆይ ወፍ ጫጩቶቿን በክንፏ እንደምትሰበስብ:: በጠላቴ ፊት ጋሻ መከታ ሁነሽ ሠውሪኝ::

ሰላም ለአእዳውኪ እሳተ መለኮት እለገሠሣ፤ አውቃፈ ብሩር ወወርቅ ለሥርጋዌሆን ኢኀሠሣ፤ ማርያም ድንግል ለመካን ህንባበ ክርሣ፤ አንጽሕኒ እግዝእትየ ለፍትወተ ዓለም እምርኵሳ፤ በዲበ ሥጋየ ኢትንበር ነጊሣ::

እመቤቴ ማርያም ሆይ እሳተ መለኮት ለዳሰሱ እጆችሽ ሰላምታ ይገባል:: እነሱም የብር አምባር የወርቅ ቀለበት ያጊያጊጣቸው ዘንድ የማይፈልጉ ናቸው:: ድንግል ሆይ የመካኒቱ የማኅፀኗ ፍሬ አንቺ ነሽ:: እመቤቴ ሆይ ከዚህ ዓለም ፍትወተ ኃጢአት ንጹሕ አድርጊኝ:: በሰውነቴ ላይ ነግሣ ትኖር ዘንድ አልሻምና::

ሰላም ለመዛርዕኪ ዘተረስያ ኃይለ ከመ ይፁራ ነበልባለ፤ ማርያም ድንግል እንተ ኀጣእኪ መምሰለ፤ ኀጢአትየ ለገብርኪ እመ ፈድፋደ ተለዐለ፤ ከመ ጥቅም ዘባቢል ረስዪ ንኡሰ::

እመቤቴ ማርያም ሆይ ኃይልን ለተቀዳጁ ወርቾችሽ ሰላምታ ይገባል:: መለኮታዊ ነበልባልን ለመሸከም ችሎታ አላቸውና:: ድንግል ሆይ ምሳሌ የማይገኝልሽ ቅድስት ነሽ:: የኔ የባሪያሽ ኃጢአት ፈጽሞ ቢበዛ እንደ ባቢሎን ግንብ ፍርስርሱን አውጭው::

ሰላም እብል ለኵርናዕኪ እዌድሶ፤ ለእሳተ መለኮት በላዒ አምጣነ ኮነ ትርአሶ፤ ማርያም ድንግል ምዕዝተ ዘእምሀንክሶ፤ ሀልዊ ደርገ ምስሌየ እንዘ አልብኪ ተግሕሦ፤

እመቤቴ ማርያም ሆይ አእዳወ ኵርማሽን (ክርንሽን) አመስግን ዘንድ ተገቢየ ነው:: ለሚያቃጥል እሳተ መለኮት መጠጊያ ተገን ሆኗልና:: ድንግል ሆይ ሐንክሶ ከሚባል ከታወቀ ሽቱ የተመረጠ

ለሕሊና ልብየ ወትረ እንግርኪ ማኅሠሥ::

መዓዛ አለሽ:: የልቤን ሀሳብ በየጊዜው እነግርሽ ዘንድ:: ያለመራቅ ሁል ጊዜ ከኔ ጋር ኑሪ::

ሰላም ለእመታትኪ እለ ጸንዓ ይፍትላ፣ ሜላተ ወወርቅ በናዝሬት ወበገሊላ፣ ማርያም ድንግል ለዮዲት ጥበበ ቃላ፣ ብጽሒ በሠረገላ ንትመሐል መሐላ፣ ከመ ታኀድርኒ በብሔር ዘተድላ::

እመቤቴ ማርያም ሆይ ከእግዚብሔር ኃይል ለፀኑ ክንዶችሽ ሰላምታ ይገባል:: በናዝሬትና በገሊላ ወርቅን ከሐር አስማምተው ሲፈትሉ ድካም አልተሰማቸውምና:: ድንግል ሆ ለዮዲት የንግግሯ መፍለቂያ የጥበብ ምንጭ ነሽ:: ተድላ ደስታ በተመላበት አገር ታኖሪኝ ዘነድ:: ፈጥነሽ በሠረገላ ነይና ቃል ኪዳን ግቢልኝ::

ሰላም ለእራኃትኪ እለ ስፉሐት ለመጥዎ፣ ስቴ መድኃኒት ጽሩየ ወእክለ አሕይዎ፣ ማርያም ድንግል እስእለኪ በተሰፍዎ፣ ከመ እክሀል በበ ፆታሁ ስብሐታተኪ ዜንዎ፣ ለገብርኪ ዓብድ ምልእኒ ለብዎ::

እመቤቴ ማርያም ሆይ ልምላሜ ወዘና ለማይለያቸው መዳፎችሽ ሰላምታ ይገባል:: የማዳን እንጀራንና የተፈተነ መድኃኒትን መጠጥን ለመስጠት ፈጥነው ይዘረጋሉና:: ድንግል ሆይ ለሁልጊዜ ተስፋ በማድረግ እማልድሻለሁ:: እየወገን እየወገኑ ምስጋናሽን እናገር ዘንድ:: ለኔ ለሰነፉ ባሪያሽ አስተዋይ ልቡናን ስጭኝ::

ሰላም ለአፃብዕኪ እምእራኃ እዴኪ እለሠረጻ፣ እምኑልቄ ሠቁስ ወስብዕ እንዘ ኢየሐጸ፣ ማርያም ድንግል ደብረ ኤልያስ ነቢየ ፋጻ፣ ዕቀብኒ በረድኤትኪ እምነ አርዌ ዘኖጻ፣ ህየንተ ሠናይ ለሰብእ ዘይሁብ ዐመፃ::

እመቤቴ ማርያም ሆይ ከቍጥር ሳይጐድሉ ሕፀፅ ሳይኖርባቸው:: ከመሐል እጅሽ ለበቀሉ (ለሠረፁ) ጣቶችሽ ሰላምታ ይገባል:: ድንግል ሆይ አርቆ የሚጠራባት ለኤልያስ የትንቢቱ ተራራ አንቺ ነሽ:: ለሰው ልጅ በበጎ ፈንታ ክፉ ከሚያስብ ተንኮለኛ አውሬ በረድኤትሽ ኃይል ጠብቂኝ::

ሰላም ለአጽፋረ እዴኪ መልዕልተ አፃብዕ እለ ሠረቃ፣ በበሕቅ ዘልፈ እንዘ ይልኀቃ፣ ማርያም ድንግል ማኀቶትየ በውስተ ጣቃ፣ ኢትሰድኒ ለገብርኪ ለዓመትየ በንፍቃ፣ ዝንቱ ውእቱ ለልብየ ጸሕቃ::

እመቤቴ ማርያም ሆይ ከቀን ወደ ቀን ጥቂት በጥቂት እያሉ ለሚያድጉ ጥፍሮችሽ ሰላምታ ይገባል:: ድንግል ሆይ የጨለማ መብራቴ እንደመሆንሽ እኔን ባሪያሽን በዘመኔ እኩሌታ አትውሰጅኝ የሌቤ ጭንቀት ይህ ነውና::

ሰላም ለአጥባትኪ እለ አውኀዛ ፍጹመ፣ ድንግልናዊ ሐሊበ ውስተ አፈ አምላክ ቅድመ፣ ማርያም ድንግል እንተ አምጻእኪ ሰላመ፣ ሕፅንኒ በአጥባትኪ ለእመ ኮንኩ ደክታመ፣ ዘእንበሌኪ ኢየኃሥሥ እመ::

እመቤቴ ማርያም ሆይ እድፍ ጉድፍ ለሌለባቸው ሁለቱ ጡቶችሽ ሰላምታ ይገባል:: የድንግልናን ወተት በአምላክ አፍ ውስጥ አመንጭተዋልና:: ድንግል ሆይ ሰላምን ያስገኘሽ የሰላም እመቤት ነሽ:: ድሀ አደግ የሆንኩ እኔን በጡቶችሽ አሳድጊኝ:: ካንቺ ሌላ (የበለጠ) እናት አልፈልግምና::

ሰላም ለገቦኪ ዘሐመልማለ ወርቅ ክዳኑ፣ በከመ ዳዊት ይዜኑ፣ ማርያም ድንግል ለያዕቆብ ሞገሰ ስኑ፣ በልኒ እግዝእትየ አፈቅረከ አኮኑ፣ እንዘ ረዳኢትከ እለ ዘይክለከ መኑ::

እመቤቴ ማርያም ሆይ ልብሷ የወርቅ መጐናፀፊያ ነው ብሎ አስቀድሞ ዳዊት እንደተናገረ:: የንጽሕናን የወርቅ አሸንክታብ ለእንገሮረገው ሽንጥሽ ሰላምታ ይገባል:: ድንግል ሆይ ለያዕቆብ ግርማ ሞገሱ ነሽ:: እኔን ባሪያሽን እወድሃለሁ እኮን:: ስለዚህ የኔ ባለሟል ስትሆን ማነው የሚደፍርህ የሚል ተስፋ ስጭኝ::

ሰላም ለከርሥኪ ዘአፈድፈደ ተበጽዖ፣ እምታቦተ ሙሴ ነቢይ ለጽሌ ትእዛዝ ዘየንብእ፣ ማርያም ድንግል ጊዜ ጸዋዕኩኪ በአስተብቍዖ፣ ለፀርየ ብእሴ ዐመፃ ኀይለ ዚአኪ ይጽብእ፣ እስከነ ያስቆቁ ጥቀ ድኅሪተ ገቢአ::

እመቤቴ ማርያም ሆይ ባለ ብዙ ብፅዕት ለሆነው ሆድሽ ሰላምታ ይገባል:: ትእዛዛተ አሪት ከተጻፉባት ከሙሴ ጽላት ይልቅ ታላቅ ክብር አለውና:: ድንግል ማርያም ሆይ ኃይልሽ የበደል ሰው የሚሆን ጠላቴን ይደመስስልኝ ዘንድ:: ለብዙ ዋይታም ዱካው እስኪጠፋ ድረስ ክንድሽ ካፈር ይደባልቀው ዘንድ:: ሁልጊዜ እማልድሻለሁ እማፀንሻለሁ::

ሰላም ለልብኪ እምነ በቀል ርጉቅ፣ አምጣነ ዐረብ ወሠርቅ፣ ማርያም ድንግል ገነተ ኅሩያን ደቂቅ፣ ክድንኒ ልብሰ ክብካብ ለቅኑይኪ ዕሩቅ፣ ከመ ጸደሬ ጽጌሁ ዘወርቅ::

እመቤቴ ማርያም ሆይ ከቂም በቀል ለሚርቅ ልቡናሽ ሰላምታ ይገባል:: ለታማኝነትሽ ፀሐይ መውጫ መግቢያ ነውና:: ድንግል ሆይ ለተመረጡና ለተባረኩ ልጆች የመዝናኛ ቦታቸው ነሽ:: ከጽድቅ ለተራቆትኩ ለኔ ለባሪያሽ የሙሽርነት ልብስ አልብሽኝ:: በወርቅ አበባ የተሠራ መጐናፀፊያን አጐናጽፊኝ::

ሰላም እብል ለኵልያትኪ ክልኤ፣ ዘቅብዐ ክህነት ቀርን ወዘወይን ትፍሥሕት ግምኤ፣ ማርያም ድንግል በልኒ ቅድመ ጉባኤ፣ ሕፃንየ በእንቲአየ ይከውነከ ረዳኤ፣ አመራደ ፀርከ ሕቀ ኢትፍራህ ትንሣኤ፡፡

እመቤቴ ማርያም ሆይ ለሁለቱ ኩልያቶችሽ ሰላም እላለሁ፡፡ የክህነት ቅብዕ ዘይትና የሚያስደስት የወይን ማጣሪያ ምርጥ ዕቃዎች ናቸውና፡፡ ድንግል ሆይ በጠላቶችህ ፊት መነሣትን አትፍራ ስለእኔ ሆኖ ልጄ ወዳጄ በጉባዔ መካከል ረዳት ይሆንሃልና በይኝ፡፡

ሰላም ለሕሊናኪ ሐልዮ ሠናያት ልማዱ፣ ወገቢረ ምሕረት መፍቅዱ፣ ማርያም ድንግል ለዳዊት ወለተ ወልዱ፣ ንዝሕኒ በአዛብኪ ዘኢይትረከብ ዘመዱ፣ ወበማየ ሕይወት ኅፅብኒ እምበረድ እጸዕዱ፡፡

እመቤቴ ማርያም ሆይ በጐ ነገር ማሰብ ልማዱ ለሆነ ኅሊናሽ ሰላምታ ይገባል፡፡ ምሕረት ማድረግ የሁል ጊዜ ተግባሩ ነውና፡፡ ድንግል ሆይ ከዳዊት ባሕርይ የተገኘሽ የዳዊት የልጅ ልጅ ነሽ፡፡ ከበደሌ እነፃ ዘንድ ምሳሌ በማይገኝለት በሐር (መነሳንስ) በሂሶጵ እርጭኝ፡፡ በሕይወት ውሃም አጥበሽ ከበረዶ የነፃሁ አድርጊኝ፡፡

ሰላም ለአማሁትኪ ለነበልባለ ኅዘን ዘአውዐዮ፣ አመ ወዐለ ወልድኪ ስቁለ በቀራንዮ፣ ማርያም ድንግል ፀምረ ጠል ዘተነብዮ፣ ጌጋይየ ለአስተሥርዮ፣ እንተ አልብኪ ተፈልዮ፣በሥርዓተ ካህን ሳዕሌየ አንኒ ጸልዮ፡፡

እመቤቴ ማርያም ሆይ ልጅሽ በቀራንዮ ተሰቅሎ በዋለ ጊዜ፡፡ በእሳት ኃዘን ለተቃጠለው አንጀትሽ ሰላምታ ይገባል፡፡ ድንግል ሆይ የትንቢት የጠል ግምጃ (መጋረጃ) ነሽ፡፡ ኃጢአትን ለማስተሥረይ መጸየፍ የሌለብሽ ነሽና፡፡ እንደ ካህን ሥርዓት ጸሎቴን አሳርጊልኝ፡፡ (አስረዝሚልኝ)

ሰላም ለንዋየ ውስጥኪ አምሳለ ንዋያ ለደብተራ፣ ስብሐተ ልዑል ዘይሤውራ፣ ማርያም ድንግል ትምክሕተ ደቂቃ ለሳራ፣ ባልሕኒ ወለተ ቅስራ፣ ለዓለመ ጽልመት እምጻዕራ፣ እስመ መቅዓን ወጠዋይ ምሕዋራ፡፡

እመቤቴ ማርያም ሆይ በደብተራ ሙሴ (በድንኳን) ለተመሰለው ውሳጣዊው ገንዘብሽ ሰላምታ ይገባል፡፡ ይህቺውም የልዑል ኃይል የሚጋርዳት ናት፡፡ ድንግል ሆይ ለሣራ ልጆች መመኪያቸው ነሽ፡፡ የቅሥራ ልጅ እመቤቴ ሆይ ከዚህች ከጨለማ ዓለም ፃዕር መከራ አድኚኝ፡፡ መንገዷ የጠበበ መተላለፊያዋም ጠማማ ነውና፡፡

ሰላም ለንዋየ ውስጥኪ አምሳለ ንዋያ ለመቅደስ፣ ንዋይኪሰ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ማርያም ድንግል ዘገዳመ ሲና ጳጦስ፣ ከመ ያነቅሖ ለልበ ዘፉኒ ናብሊስ፣ ፍቅርኪ ያንቅሕኒ በሥጋ ወነፍስ፡፡

እመቤቴ ማርያም ሆይ በንዋየ መቅደስ ለሚመሰል ውሳጣዊ ገንዘብሽ ሰላምታ ይገባል፡፡ ይኸውም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ድንግል ሆይ ነደ እሳት ያላቃጠላት በሲና በረሀ ዕፅ እንመስልሻለን፡፡ ያዝማሪን ልብ የሙዚቃ ድምፅ እንደሚያነቃቃው፡፡ እኔንም እንዲሁ በነፍስ በሥጋ መንፈሳዊ ድምፅሽ ያንቃኝ፡፡

ሰላም ለኅንብርትኪ ከመ ማዕከክ ርእየቱ፣ ዘኢየዐርቅ እምቱስሕቱ፣ ማርያም ድንግል ለካህን ዕፀ ኅርየቱ፣ ከመ ኢይኩን ጽሩዐ ንባበ አፉየ ዝንቱ፣ በጽዋዐ ኪሩብ ደዪዮ ወሡጢዮ ሎቱ፡፡

እመቤቴ ማርያም ሆይ አቀማመጡ እንደብር ጉትቻ (ፈርጥ) ለሆነ ሕንብርትሽ ሰላምታ ይገባል፡፡ እሱም ክህልውናው የማይታረዝ ነው፡፡ ድንግል ሆይ ሳይተክሏት የበቀለች ውሃ ሳያጠጧት የለመለመች የአሮን የምርጫ በትሩ አንቺ ነሽ፡፡ በምጸልይ ጊዜ የአፌ አነጋገር ጉድለት ቢገኝበት፡፡ በኪሩብ ጽዋ አንቺ ሙይበት፡፡

ሰላም ለማኅፀንኪ ለእግዚአብሔር ማኅፈዱ፣ ዘሐነጸኪ የማነ እዱ፣ ማርያም ድንግል ምእዝት ዘእምናርዱ፣ ኅቤኪ ያንቀዐዱ ለረኪበ ኵሉ መፍቅዱ፣ ምስለ ካልኡ ዐይንየ አሐዱ፡፡

እመቤቴ ማርያም ሆይ የእግዚአብሔር ማደሪያ ለሆነው ማኅፀንሽ ሰላምታ ይገባል፡፡ የእግዚአብሔር ቀኝ እጁ ያበጃጀሽ (ያከናወነሽ) ነሽና፡፡ ድንግል ሆይ ናርዱ ከሚባል ሽቱ እጅግ ብልጫ ያለው መዓዛ አለሽ፡፡ እመቤቴ ሆይ የፈለገውን ሁሉ ለማግኘት አንዱ ዓይኔ ከሁለተኛው ጋር ወደ አንቺ ያንጋጥጣል፡፡

ሰላም ለማኅፀንኪ ለእግዚአብሔር ዘውጉ፣ ብዑድ ሥርዐቱ ወፍሉጥ ሕጉ፣ ማርያም ድንግል ለአስካለ ሕይወት ሐረጉ፣ በልኒ እግዝእትየ ኀጢአተከ ኀደጉ፣ ወመኃልየከ ሰማየ አዕረጉ፡፡

እመቤቴ ማርያም ሆይ የእግዚአብሔር መቅደስ ለሆነ ማኅፀንሽ ሰላምታ ይገባል፡፡ ሕጉና ሥርዓቱ ከሌሎች የተለየ ነውና፡፡ ድንግል ሆይ የሕይወት ወይን ሐረግ እየተባልሽ ስትመሰገኚ ትኖሪያለሽ፡፡ እመቤቴ ሆይ ኃጢአትህ ተሠረየችልህ በይኝ፡፡ ወደ ሰማይ አሳረግሁልህ በይኝ፡፡

ሰላም እብል ለድንግልናኪ ዕጽው፣ እንተ እምኔሁ ሠረቀ ፀሐየ መለኮት ኅትው፣ ማርያም ድንግል ዘስነ ንጽሕኪ ፍትው፣ ለኅዲር በበፍናው በአህጉር ወበድው፣ዕቀብኒ ወለቶሙ ለኄራን አበው።

እመቤቴ ማርያም ሆይ ለነቱም ድንግልናሽ ሰላምታ ይገባል። ከርሱ ፀሐየ ጽድቅ የተባለ ኢየሱስ ክርስቶስ ተገኝቷልና። ድንግል ሆይ የንጽሕና ደም ግባትሽ በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደደ ነው። የኒያ የደጋጎች አባቶች ልጅ እመቤቴ ሆይ ሩቅ ጉዳና በምንዝበት ጊዜ ባደርኩበት ቦታ ሁሉ ጥበቃሽ አይለየኝ።

ሰላም ለሐቌኪ በትረ ሌዋዊ ሣውዕ፣ ዘኢሐፀነኪ ጠል ወዘኢሠቀየኪ ነቅዕ፣ ማርያም ድንግል እግዝእተ መላእክት ወሰብእ፣ ለድኒ ብሔር ፍግዕ በትንባሌኪ ባቍዕ፣ ምስለ ኅሩያንኪ ደርገ አሀሉ በስንዕ።

እመቤቴ ማርያም ሆይ በትረ ሌዋዊ (አሮን) እየተባለ ለሚጠራው ወገብሽ ሰላምታ ይገባል። ጠል ሳያሳድግሽ ምንጭ ሳያጠጣሽ ለምልመሽ ተገኝተሻልና። ድንግል ሆይ የሰውና የመላእክት እመቤታቸው ነሽ። ከተመረጡ ወገኖችሽ ጋር አብሬ እኖር ዘንድ። በጽኑ ረድኤትሽ ተድላ ደስታ ወዳለበት ቦታ መርተሽ ውሰጅኝ።

ሰላም ለአቍያጽኪ እለ ይነብራ ድርገተ፣ እምነ አብራክኪ ላዕለ ወእምነ ሐቌኪ ታሕተ፣ ማርያም ድንግል እንተ ኢተአምሪ ርስሐተ፣ ጽባሕ ወምሴተ ኵሎ ዕለተ፣ ዘይሰማዕ ምሕረተኪ ግበሪ ሊተ።

እመቤቴ ማርያም ሆይ ሳይነጣጠሉ ለሚኖሩ አቍያጾችሽ ሰላምታ ይገባል። የዚህ ዓለም ፈተና ክቶ ሊፈታተናቸው አይቻለውምና። ድንግል ሆይ ርስሐተ ኃጢአት የሌለብሽ ፍጽምት ነሽ። ሁል ጊዜ ለጧት ለማታ ቸርነትሽ ፈጽሞ ይደረግልኝ።

ሰላም ለአብራክኪ በስብሐተ ልዑል ዘአስተብረካ፣ እምአመ ወሀቡኪ ብፅዐ ውስተ ኦሪታዊት ታዕካ፣ ማርያም ድንግል መንበር ዘእብነ ፔካ፣ ጊዜ ለደቶሙ ለኃጥአን አምዓጸደ ፀባይ ፋሲካ፣ ዔውውኒ መንገሌኪ እኩንኪ ምህርካ።

እመቤቴ ማርያም ሆይ ለእግዚአብሔር ብፅአት አድርገው ወደ ቤተ መቅደስ ባስገቡሽ ጊዜ። ለልዑል ምስጋና ለተንበረከኩ ጉልበቶሽ ሰላምታ ይገባል። ድንግል ሆይ የዕንቍ ደንጊያ መንበር ነሽ። ኃጥአን ከታላቅ የደስታ አደባባይ በተሰደዱ ጊዜ ምርኮ እሆንሽ ዘንድ ከነሱ ለይተሽ አስቀሪኝ።

ሰላም ለእኢጋርኪ እለ ጻመዋ በረዊጽ፣ እምቤተ ልሔም ዘይሁዳ እስከ ምድረ ግብጽ፣ ማርያም ድንግል ሥርጉተ ነበልባል ዕፅ፣ ለኅዲር በቤተ ናሕስ እንተ መልዕልተ ኰኩሕ ሕኑጽ፣ አጥብብኒ በተግሣጽ ወሱቅኒ እምዳኅፅ።

እመቤቴ ማርያም ሆይ የይሁዳ ክፍለ ሀገር ከምትሆን ከቤተ ልሔም እስከ ምድረ ግብፅ ድረስ በሩጫ ለደከሙ እግሮችሽ ሰላምታ ይገባል። ድንግል ሆይ ነደ እሳት የማያቃጥላት በነበልባል ያጌጥሽ ዕፅ ነሽ በጭንጫ ላይ በታነፀ ፎቅ ለመኖር እችል ዘንድ። በእውቀት ከፍ ከፍ አድርጊኝ እንዳልወድቅም ደግፊኝ።

ሰላም እብል ለዘኪአኪ ለኵና፣ ዘኢድኀፀ በውስተ ፍና፣ ማርያም ድንግል ትምእርተ ኪዳን ቀስተ ደመና፣ እምዕዝኒ በዕፍረትኪ ወጸግወኒ ጥዒና፣ በከመ ትገብር እም ለንኡስ ሕፃና።

እመቤቴ ማርያም ሆይ ለእግር ተረከዝሽ ሰላምታ ይገባል። በመንገድ ላይ ድጥ አያዳልጠውምና። ድንግል ሆይ ለኖኅ የቃል ኪዳኑ ምልክት ቀስተ ደመና ነሽ እናት ለሕፃን ልጅዋ እንደምታደርግለት በጣፈጠ ሽቱ አጣፍጠሽ ጤንነትን ስጪኝ።

ሰላም ለመከየድኪ እለ ረከቦን መከራ፣ እምፍርሃተ ቀተልት ሐራ እንበለ አሣእኑ እመ ሖራ፣ ማርያም ጽዮን ታቦተ ቃለ ጽድቅ መንፈቀ ዕሥራ፣ ዕገላት እምዕገሊሆን ከመ ኪያኪ አፍቀራ፣ አፍቀርኩኪ አፍቅርኒ እምይእዜ ለግሙራ።

እመቤቴ ማርያም ሆይ ብዙ መከራ ላገኛቸው ጫማዎችሽ ሰላምታ ይገባል። ከነፍስ ገዳዮች ከሄሮድስ ወታደሮች ፍርኃት የተነሣ ያለጫማ በእሾክና በበረሃ ረሞጫ ላይ ተጉዘዋልና።

እውነተኛው የእግዚአብሔር ቃል (ዐሠርቱ ቃላት) የተጻፉብሽ የሙሴ ታቦት (ጽላት) ነሽ። (ጊደሮች) ርግቦች ከልጆቻቸው ይልቅ አንቺን እንደወደዱ። ከዛሬ ጀምሮ ፈጽሜ አፈቅርሻለሁና ረድኤትሽ አይለየኝ።

ለአጻብእኪ

እመቤቴ ማርያም ሆይ ስድስትና አራት ተደምሮ ዓሥር ለሚሆኑ ለእግር ጣቶችሽ ሰላም እላለሁ። ድንግል ሆይ ንጹሕ የመሠዊያ መንበር የተባልሽ ነሽ። አፌ ስምሽን በጠራ ጊዜ በሩጫና በችኮላ ፈጥነሽ ድረሽልኝ።

ሰላም እብል ዘአእጋርኪ አፃብዐ፣ ሐሳበ ኍልቆን ዘኮነ ምስለ ስድስ ርብዐ፣ ማርያም ድንግል ዘተሰመይኪ ምሥዋዐ፣ በረዊጽ ወበጕጕዓ፣ አፍጥኒ መጺአ ሶበ አፉየ ስመኪጸውዐ::

ሰላም ለአጽፋረ እግርኪ ዘኢፈቀዳ ለሥርጋዌ፣ ጥምዐታተ ኅምር ምድራዌ፣ ማርያም ድንግል ሐውልተ ስምዕ ዘወልደ ነዌ ሠቅኒ፣ እምትንታኔ ወባልሕኒ እምአርዌ፣ ላዕለ እምየ ዘአምጽአ ደዌ::

እመቤቴ ማርያም ሆይ በመንፈስ ቅዱስ ለተጌጡ የእግር ጥፍሮችሽ ሰላምታ ይገባል:: እንሶስላ ሞቀው ማጌጥን አልፈቀዱምና:: ድንግል ሆይ የነዌ ልጅ የኢያሱ የመታሰቢያው ሐውልት ነሽ:: ከአዳኝ አውሬ በዲያብሎስ ግፊት እንዳልወድቅ ደግፊኝ ቀድሞ በእናቴ በሔዋን ላይ ታላቅ መከራ ያመጣባት እሱ ነውና::

ሰላም ለቆምኪ በቀልተ ዘተመሰለ፣ ኀበ ሙኀዘ ማይ ዘበቈለ፣ ማርያም ድንግል እስእለኪ ስኢለ፣ ኢይረድ ታሕቲተ ምጥቅኒ ላዕለ፣ ኢረከብኩ በርኅራኄ ከማኪ ዘብዕለ::

እመቤቴ ማርያም ሆይ በምንጭ ዳርቻ እንደበቀለና የዘንባባ ዛፍ ለሚመስለው ቁመናሽ ሰላምታ ይገባል:: ድንግል ሆይ ልመናዬን ትሰሚኝ ዘንድ እማልድሻለሁ:: ወደታች እንዳልወርድ ወደ ላይ አውጭኝ:: በርህራኄ የበለጸገ እንዳንቺ አላገኘምና::

ሰላም ለመልክዕኪ ዘተሠርገወ አሚረ፣ ዘያበርህ ወትረ ፍቅርትየ አንቲ እንተ ታብድሪ ፍቅረ፣ አርእይኒ ገጸ ዚአኪ ማርያም ምዕረ፣ ዘኢይሰምዖ ካልእ አንግርኪ ነገረ

እመቤቴ ማርያም ሆይ እንደ ፀሐይ ለሚያበራው መልክሽ ሰላምታ ይገባል:: የፀዳሉ ብርሃን ሁልጊዜ አይጐድልበትምና:: ድንግል ሆይ የፍቅር ባለቤት ሰላም ወዳድ ነሽ:: ፍጹም የሆነ ብርሃንን የተመላ ፊትሽ ይገለጥልኝ:: ማንም ሊሰማው የማልፈልገው የማሳስብሽ ነገር አለኝና::

ሰላም ለፀአተ ነፍስኪ እንበለ ፃዕር ወጻማ፣ ለነቢር ዘልፈ በየማነ ወልድኪ ፌማ፣ ማርያም ድንግል ክልልተ ሞገስ ወግርማ፣ አጽንዒ በረድኤትኪ ለሕይወትየ ድካማ፣ እምሕይወተ ኄራን አበው ኢታሕጽጺ ዐቅማ::

እመቤቴ ማርያም ሆይ ያለመጨነቅና ያለፃዕር ከሥጋዋ ለተለየች ነፍስሽ ሰላምታ ይገባል:: አነዋወሯም በልጅሽ ቀኝ ጐን በክብር ነው:: ድንግል ሆይ ከፈጣሪ ዘንድ የባለሟልነትን ግርማን የተጐናፀፍሽ ነሽ:: በረድኤትሽ ሰውነቴን ከድካሟ አሳርፊያት ክብሯም (ኃይሏም) ከደጋግ አባቶቿ ክብር (ኃይል) ያነሰ አይሁን::

ሰላም እብል በድነ ሥጋኪ ጽሩየ፣ ዘተመሰለ ባሕርየ፣ ማርያም ድንግል ዐጸደ ወይንየ፣ ንስቲተ ለዕበይኪ እንተ አቅረብኩ ግናየ፣ ኢይትኀደግ ዲበ ምድር ምሥጢ ሰማየ::

እመቤቴ ማርያም ሆይ እንደ ዕንቍ ለከበረ በድነ ሥጋሽ ሰላም እላለሁ:: ከወርቅና ከብር ይልቅ የተለየ የጥራት ባሕርይ አለውና:: ድንግል ሆይ የወይን ተክል ቦታዬ ነሽ እኮን:: ለገናናው ስምሽ ያቀረብኩት አነስተኛ ምስጋና:: በምድር እንዳይቀር ወደ ሰማይ አሳርጊልኝ::

ሰላም ለግንዘተ ሥጋኪ በእደ ሐዋርያት አርጋብ፣ በአፈወ ዕፍረት ቅድው ዘሐሳበ ሤጡ ዕጹብ፣ ማርያም ድንግል ወለተ ኅሩያን ሕዝብ፣ ረሰይኩኪ እግዝእትየ ህየንተ እም ወአብ፣ ይሕፅነኒ ከመ ጥብ ፍቅርኪ ሐሊብ::

እመቤቴ ማርያም ሆይ ዋጋው እጅግ ብዙ በሆነና መዓዛው በሚጣፍጥ ሽቱ:: በሐዋርያት እጅ ለተገነዘው ንጹሕ ሥጋሽ ሰላምታ ይገባል:: ድንግል ሆይ የተመረጡና የተባረኩ ወገኖች የሆኑ ቡርክት ልጅ ነሽ:: እመቤቴ ሆይ ቸርነትሽ እንደጡት ሆኖ ያሳድገኝ ዘንድ:: አንቺን እንደ እናት አባት አድርጌሻለሁና::

ሰላም ለመቃብርኪ ለጌቴሴማኒ በመርኅባ፣ እንተ ይእቲ ለኢየሩሳሌም ቅሩባ፣ ማርያም ድንግል ለህገረ መንግሥት ርግባ፣ ትትሜጦ ወርቀ እምአፌር ወጸበለ አፈው እምሳባ፣ ጌቴሴማኒ ለሥጋኪ ምስካባ::

እመቤቴ ማርያም ሆይ ጌቴ ሰማኒ ለምትባል መካነ መቃብርሽ ሰላምታ ይገባል:: ይኸችም ለኢየሩሳሌም አቅራቢያዋን አፋዛኟ ናት:: ድንግል ሆይ ርግበ መንግሥተ ሰማይ እየተባልሽ ትመሰገኛለሽ:: የሥጋሽ ማረፊያ ለሆነች ጌቴ ሰማኒም ከላባ የሽቱ አፈር ከአፌር የወርቅ ሐውልት ይቀርብላታል::

ሰላም ለመቃብርኪ ለኢየሩሳሌም በአድያማ፣ እንተ ይእቲ ጌቴሴማኒ ስማ፣ ማርያም ሰንበት ዕረፍተ ጽዑራን እምጻማ፣ አመ ኀደረ ላዕሌኪ ፀሐየ ቅዱሳን ዘራማ፣ ኀይለ ልዑል ጸለለኪ በመንክር ግርማ::

እመቤቴ ማርያም ሆይ አሁንም በኢየሩሳሌም አውራጃ ለምትገኘው መካነ መቃብርሽ ሰላምታ ይገባል:: ይኸችውም ስሟ ጌቴ ሰማኒ ይባላል:: ድንግል ሆይ በመንፈስ ለተጨነቁትና በሐሳብ ለደከሙት የዕረፍት ቀናቸው ነሽ:: ብርሃነ ቅዱሳን የተባለ ፀሐየ ጽድቅ ኢየሱስ ክርስቶስ ባንቺ ላይ ባደረ ጊዜ የልዑል ኃይል በታላቅ ግርማ ጋረደሽ::

ሰላም ለፍልሰተ ሥጋኪ መካነ ፍሥሐ ምጡቀ፣ በአእባነ ባሕርይ ዘተነድቀ፣ ማርያም ደብተራ እንተ ኢትትከደኒ ሠቀ፣ ጽሒፈ ውዳሴኪ እምኢኀልቀ ሶበ ኮነ ጥቀ፣ ዝናመ ክረሞት ቀለመ ወሰማየ ረቀ።

እመቤቴ ማርያም ሆይ ምጡቅና ሩቅ ወደሚሆን የደስታ ቦታ ላረገ ሥጋሽ ሰላምታ ይገባል። ይኸውም ኅብሩ ሊመረምሩት በማይቻል ዕንቍ የታነፀ ሕንፃ ይገኝበታል። ድንግል ሆይ የማቅና የጨርቅ ያይደለ የብርሃን ድንኳን ነሽ። የክረምት ዝናም ቀለም ሰማያት ወረቀት ቢሆኑ ምስጋናህ ተጽፎ የሚያልቅ አይደለም።

ሰላም ለፍልሰተ ሥጋኪ ወለተ ንጉሥ ይሁዳ፣ ወወለተ ሌዊ እንትሁ ዘሀብተ ክህነቱ አገዳ፣ ማርያም ድንግል ምዕዝት ዘእምጽጌረዳ፣ በጽሒፍ ኢይፌጽሞ ለስብሐትኪ እንግዳ፣ እመ ኮነ በቅድሜየ ሰፍሐ ምድር ሰሌዳ።

እመቤቴ ማርያም ሆይ አሁን የንጉሥ ይሁዳ ልጅ ሆይ ከመሬት ወደ ሰማይ ላረገው ሥጋሽ መገኛ ሰላምታ ይገባል። የክህነቱ ሀብት መገኛ የወንድሙ የሌዊ ልጅ ሆይ ላንቺ ክብር ይገባሻል። ድንግል ሆይ መዓዛሽ ከጽጌ ረዳ ሽታ ይበልጣል የምድር ስፋት በሰሌዳ መልክ ቢዘጋጅ። እያደር አዲስና እንግዳ የሚሆን ምስጋናሽን ፍጡር ጽፎ ሊጨርሰው አይችልም።

ሰላም ለፍልሰተ ሥጋኪ ደባትረ ብርሃን ኀበ ተተክሉ፣ ለገነተ ጽባሕ በማእከሉ፣ ውድስት አንቲ ወስብሕት በአፈ ኵሉ፣ እምነ ጻድቃን ዘታሕቱ ወእምትጉሃን ዘላዕሉ፣ ማርያም ለኪ ስብሐተ አደሉ።

እመቤቴ ማርያም ሆይ በምሥራቃዊ ተክለ ገነት መካከል የብርሃን ድንኳኖች ወደ ተተከሉበት ለዐረገ ሥጋሽ ሰላምታ ይገባል። ድንግል ሆይ በሁሉ አንደበት መመስገን የተገባሽ ስለሆነ። በሰማይ ካሉ መላእክትና በምድር ከሚኖሩ ደቂቀ አዳም። ሁልጊዜ ምስጋና ይቀርብልሻል።

በዝንቱ ቃለ ማኅሌት ወበዝንቱ ይባቤ፣ ለዘይስእለኪ ብእሲ ጊዜ ረከቦ ምንዳቤ፣ ብጽሒ ፍጡነ ትስጠዊዮ ዘይቤ፣ ማርያም ዕንቍየ ክርስቲሎቤ፣ ወምዕዝተ ምግባር እምከርቤ፣ ዘጸገየ ማኅፀኪ አፈወ ነባቤ።

እመቤቴ ማርያም ሆይ በዚህ የምስጋና ቃል በዚህ የይባቤ ድምፅ የሚያመሰግንሽ ሰው። መከራ ባገኘው ጊዜ ፈጥነሽ ድረሽለትና አይዞህ አለሁልህ በይው። ድንግል ሆይ ክርስቲሎቤ የተባለ ዕንቍ ፈርጥ ነሽ። ሥነ ምግባርሽም ከከርቤ መዓዛ የተለየ ነው። ማኅፀንህ ነባቢነት ያለውን የሽቱ አበባ አስገኝቷልና።

ስብሐት ለኪ ማርያም በኵልቄ ኵሉ ሥዕርትየ፣ ስብሐት ለኪ ማርያም በኵልቄ ኵሉ አዕፅምትየ፣ ስብሐት ለኪ ማርያም በኵልቄ ኵሉ ዘተርእየ፣ ስብሐት ለኪ ንግሥትየ በኵልቄ ኵሉ ዘኢያስተርእየ፣ ስብሐተ ድንግልናኪ ዘልፈ ይነግር አፉየ።

እመቤቴ ማርያም ሆይ በራስ ፀጉሬ ቍጥር አመሰግንሻለሁ። በአጥንቶቼም ቍጥር አመሰግንሻለሁ። ድንግል ሆይ በሚታየውና በሚዳሰሰው ሁሉ ቍጥር አመሰግንሻለሁ። ንግሥት ሆይ በማይታየውና በማይዳሰሰው ሁሉ ቍጥር ሰላም እያልሁ የድንግልናሽን ምስጋና አፌ ሁል ጊዜ ይናገራል። እስከዘላለሙ አሜን።

እግዚብሔር ኀቤኪ ፈነወ ቃሎ፣ ገብርኤልሃ አስተማሲሎ፣ ማርያም አምላክ ዘወለድኪ በተደንግሎ፣ ሰላም ሰላም ወሰላም እብሎ ለመልክዕኪ ፈጺምየ ኵሎ።

ለዘኢያፈቅረኪ እግዝእትየ ማርያም ውኩፈ ኢይኩን ጸሎቱ፣ ይትገዘም ኑኀ ዓመቱ ወይጥፋእ በከንቱ፣ በአፈ መላእክት ወሰብእ ይትረገም ለለሰዓቱ፣ ዘአስተማሰሎ በተውኔት ለማኅሌተ ንግሥኪ ዝንቱ፣ ጌጋዩ ወኃጢአቱ ኢይትኃይደግ ሎቱ።

ኦ እግዝእትየ ማርያም ዕቀብኒ ወአድኅንኒ እመከራ ሥጋ ወነፍስ ሊተ ለገብርኪ